# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የብሔራዊ (አገር ውስጥ) ጨረታ የዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ሞዴል መደበኛ የጨረታ ሰነድ እና የዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ግዥ ፎርም

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ሰኔ/2003

ባህርዳ

# I የዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ ሞዴል የመደበኛ የጨረታ ሰነድ

## ማውጫ

ርዕስ

ገጽ


የጨረታ ማስታወቂያ ......1
ክፍል 1.የተጫራቾች መመሪያ------2
2. የጨረታ ሰነድ ስለማሻሻል ......3
3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና / ቢድ ቦንድ/......3
4. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ ......4
5. የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ......5
6. ጨረታን መክፈት፣ መገምገምና አሸናፊውን መለየት ......5
7. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ ......6
8. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ......7
9. የጨረታ ውጤትን ስለመግለፅ እና የውል ስምምነት ስለመፈፀም ......7
10. የግዥ ውል ማስከበሪያ /ፐርፎርማንስ ቦንድ/ ......8
11. የርክክብ ጊዜና ቦታ ......8
12. አቤቱታ ስለማቅረብ ......9
ክፍል 2. የውል አጠቃላይ ሁኔታ ------9
1. ትርጓሜ......9
2. ምርመራና ሙከራ ......10
3 አገልግሎቶች ......10
4. የዋስትና ኃላፊነት ......11
5. ክፍያ......11
6 ዋጋ ......11
7 . የውል ማሻሻል ......11
8. ግዴታን ስለማስተላለፍ ......12
9 የአቅራቢው አፈፃፀም መዘግዬት ......12
10 የጉዳት ካሳ......12
11 ውልን ስለማቋረጥ......13
12 ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ......13
13 አለማግባባትን ስለመፍታት ......13
14 ስለ ቋንቋ......13
15 ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች ......14
ክፍል 3. የዕቃ አቅርቦት ውል------14
ክፍል 4. የጨረታ ቅጾች ------20
1. የግዥ ፍላጎት ማቅረቢያ ቅጽ ......20
2. የመወዳደሪያ ሃሣብ ስለማቅረብ......21
3. የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ......22
4. የጨረታ ማወዳደሪያ ቅጽ......23
5. የአሸናፊነት የጥሪ ማስታወቂያ......24
6. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ቅጽ......25
7. የግዥ ውል ማስከበሪያ ዋስትና ቅጽ ......26
8. ለቅድሚያ ክፍያ የባንክ ዋስትና ቅጽ ......27
ክፍል 5 የእቃ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ዝርዝር (Specification) ናሙና------28

*የጨረታ ቁጥር-------------------*

*ቀን-------------------------*

# *የጨረታ ማስታወቂያ*

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ------------------------ቢሮ/ባለስልጣን/ኤጀንሲ/ጽ/ቤት ----------ዞን የ-----------------መምሪያ የ-----------------ወረዳ የ-------------ጽ/ቤት ለ-----------------አገልግሎት የሚውሉ አቅርቦቶችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል። ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ይጋብዛል።

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣
2. የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅርብ የሚችሉ፣
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው፣
4. የግዥው መጠን ብር 100,000.00 /መቶ ሺህ ብር/ እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ (VAT) ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
5. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ በተ.ቁ 1-4 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
6. የሚገዙ የዕቃዎችን ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ (ስፔስፊኬሽን) ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይቻላል፣
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር-----/-------------------/ በመክፈል ከ----------ክፍል ቢሮ ቁጥር-----ማግኘት ይቻላል፣
8. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) ለሚወዳደሩበት ብር----------ወይም የዕቃውን ጠቅላላ ዋጋ ----% በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ (ሲ.ፒ.ኦ) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ አለባቸው፣
9. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሃሳቡን በአንድ ወይም አንድ ወጥ በሆኑ ሁለት ቅጂዎች ማለትም ዋናና ቅጂ በማለት በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ በ-----------------ቢሮ/መምሪያ/ጽ/ቤት በ--------ሂደት ወይም ቢሮ ቁጥር-------- በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በሥራ ሰዓት እስከ ------ቀን ------ዓ.ም ------ ሠዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፣
10. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ--------------ክፍል በቢሮ ቁጥር------ በ------------ቀን --------ዓ.ም በ------ሠዓት ይከፈታል፣
11. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፣
12. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር ------ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በፋክስ ቁጥር ---------በመላክ ወይም በስልክ ቁጥር -----------በመደወል ማግኘት ይችላሉ፣

**ከሠላምታ ጋር**

የመ/ቤቱ ማህተም ይስፈርበት

# ክፍል 1.

# የተጫራቾች መመሪያ

## 1. ጠቅላላ

1.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የ------------------------ ቢሮ/ባለስልጣን/ኤጀንሲ/ጽ/ቤት የ----------ዞን የ------------------መምሪያ የ------------------ወረዳ የ-------------ጽ/ቤት ስልክ ቁጥር-----------ፋክስ ቁጥር---------የሚገዛቸው ዕቃዎች/አገልግሎቶች ------------------ ናቸው።

1.2 ተጫራቾች ዕቃዎችን/አገልግሎቶችን ለማቅረብ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያወጡ፣ የተሰጣቸው ፈቃድ አንድ ዓመት የሞላው ከሆነ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን አለባቸው፤

1.3 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት እና ግዥው መጠን ብር 100,000.00 /መቶ ሺህ ብር/ እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ (VAT) ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፣

1.4 ተጫራቾች ከአሁን በፊት የመንግስት ግዥዎች ላይ ተሳትፈው አሸናፊ መሆናቸው ተገልፆላቸው ቀርበው ውል ለመያዝ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ወይም ውል ይዘው በአግባቡ ባለመፈፀማቸው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የተወሰደው እርምጃ በማስረጃ የተደገፈ መሆን አለበት፣

1.5 በጨረታው ለመሣተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር------/-----------------/ በመክፈል የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከሚዘጋበት ቀን ድረስ መ/ቤቱ ወይም ጽ/ቤት በመቅረብ ዘወትር በሥራ ሠዓት መውሰድ ይችላሉ፤

1.6 ተጫራቾች ለዕቃው ዓይነትም ሆነ መጠን በጨረታው በሙሉ ወይም በከፊል መሣተፍ ይችላሉ። ሆኖም አንድ ተጫራች በአንድ ሎት ውስጥ ከተዘረዘሩት የዕቃ ዓይነቶች መካከል ከፋፍሎ መጫረት አይቻልም፤

1.7 በጨረታው ለመሳተፍ ወይም ለመወዳደር የሚወጡ ወጭዎች ቢኖሩ መ/ቤቱ ተጠያቂ አይሆንም፣

1.8 ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ማንኛውንም ዓይነት ግብር የሸፈነ መሆን አለበት፣

1.9 መ/ቤቱ የዕቃዎችን ዓይነት ናሙና የሚፈልግ ከሆነ ተጫራቾች የተጠየቁትን ናሙና እስከ ----ቀን ---ዓ.ም ድረስ በ--------ክፍል ቢሮ ቁጥር--------ማቅረብ አለባቸው፤

1.10 ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውንና ደጋፊ ማስረጃቸውን የሚያዘጋጁበት ቋንቋ በአማረኛ መሆን ይኖርበታል፤

1.11 ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በጨረታ ማስታወቂያው በተገለፀው ቦታ፣ ቀንና ሰዓት መሠረት ማስገባት ይኖርባቸዋል። ሆኖም የመጫረቻ ሰነዶች ብዛት

ያላቸው በመሆናቸው በጨረታ ሳጥኑ ማስገባት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ለ---------------------- ማስረከብ ይችላሉ። ተረካቢውም የተጫራቹን ሥምና አድራሻ እንዲሁም የተረከበበትን ቀንና ሠዓት የሚገልፅ ማስረጃ/ደረሰኝ ይሰጣል፤

1.12 አንድ ተጫራች በወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ ጥያቄ ወይም ማብራሪያ ቢያስፈልግ ጨረታውን ላወጣው መ/ቤት በጽሁፍ ወይም በፋክስ ቁጥር------------ማቅረብ ይችላል። ጨረታውን ያወጣው መ/ቤትም ለተጠየቀው ጥያቄ ማብራሪያ የሚያሰጥ ሆኖ ሲገኝ ለሁሉም ተጫራቾች በጽሁፍ ወይም በፋክስ ጨረታው ከመከፈቱ -------ቀናት በፊት መልስ ይሰጣል፤

1.13 መ/ቤቱ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

1.14 በተጫራቾች መመሪያ ይዘት ላይ ምንም ማሻሻያ ማድርግ አይቻልም።

## 2. የጨረታ ሰነድ ስለማሻሻል

2.1. ጨረታውን ያውጣው መ/ቤት ጨረታው ከመዘጋቱ ------------ቀናት በፊት በማናቸውም ጊዜና ሠዓት በራሱ ወይም የጨረታ ሰነዱን በገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻነት የጨረታ ሰነዱን ማሻሻል ይችላል፣

2.2. የተደረገው ማሻሻያ የጨረታ ሰነዱ አካል የሚሆን ሲሆን በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ሰነዱን ለገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች እና በቀጣይ ሰነዱን ለሚገዙ ሁሉ በተገቢው ሁኔታ በእኩል እንዲደርስ ይደረጋል፣

2.3 በጨረታ ሰነዱ ማሻሻያ መሠረትም መ/ቤቱ የጨረታ መክፈቻ ጊዜውን እንደ አስፈላጊነቱ ለ---------ቀናት ለአንድ ጊዜ ብቻ ያራዝማል፣

2.4 ተጫራቾች ቀደም ሲል ባስገቡት የጨረታ ዋጋ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በልዩ ሁኔታ መቀነስ ቢፈልጉ ካቀረቡት ጠቅላላ ዋጋ የሚቀንሱትን መጠን በመቶኛ /በ%/ የጨረታው ሣጥን ከመዘጋቱ ----ቀን በፊት ማስገባት ይችላሉ። ሆኖም የጨረታ ሰነዱን ይዘት መቀዬር አይችሉም።

## 3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና / ቢድ ቦንድ/

3.1 ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት ብር --------/----------------ብር/ ወይም ጠቅላላ የዕቃ/የአገልግሎት ዋጋ-----% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድቦንድ) በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ (ሲ.ፒ.ኦ) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና /Unconditional Bank Garntee/ ከዋጋ ማቅረቢያው ጋር በጥንቃቄ በታሸገ በፖስታ ማቅረብ ወይም ጥሬ ገንዘብ በመ/ቤቱ በህጋዊ ደረሰኝ ማስያዝ አለባቸው፤

3.2. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 20 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል።

3.3. ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ተከፍቶ አሸናፊው ከተለዬና ውል ከተያዘ ጀምሮ ባሉት በ6 ወራት ውስጥ መውሰድ አለባቸው።

3.4. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በሚከተሉት ምክንያቶች ይወረሳል።

ሀ. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድር ካገለለ፣

ለ. አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለፀበት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ፣

ሐ. አሸናፊው እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ ካላቀረበ፣

መ. የጨረታ አሸናፊው ተለይቶ ውል ከተያዘ በኋላ ተሸናፊው ተጫራች ዋስትናውን እንዲወስድ በጽሑፍ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ 6 ወራት ውስጥ ያልወሰደ ተጫራች፣

ሠ. ተጫራቹ ጨረታውን ለማዛባት የሞከረ መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ፣

3.5. ከላይ በተ.ቁ 3.4 (ሀ-ሠ) የተመመለከቱትን የፈፀመ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ሙሉ ለሙሉ የሚወረስበት ሲሆን በህግም ሊጠየቅ ይችላል፤

## 4. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ

4.1. ተጫራቾች አስፈላጊ መረጃዎች ፎቶኮፒ እና የሚያቀርቡበትን የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተውን የዕቃ ዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ በመጠቀም በተገለፀው ዝርዝር መግለጫ /ስፔስፊኬሽን / መሠረት ስርዝ ድልዝ በሌለበት ሁኔታ ተለይቶ በዝርዝር በመሙላት፣ በመፈረምና በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተም በማድረግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።ስርዝ ድልዝ ካለም ስለመስተካከሉ ፓራፍ መደረግ አለበት።

4.2. ተጫራቾች በዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ በተመለከተው መሠረት የእያንዳንዱን ዕቃ/አገልግሎት ብዛት ነጠላ ዋጋና ጠቅላላ ዋጋ መግለፅ አለባቸው፣

4.3. ተጫራቾች የመጫራቻ ሰነዶቻቸውን በአንድ ወይም አንድ ወጥ በሆኑ ሁለት ፖስታዎች በጥንቃቄ አሽገውና ማህተም አድርገው ያቀረባሉ። የሚፈለገው ፖስታ በሁለት ቅጂ ከሆነ በፖስታው ላይ ዋናውንና ቅጂውን በጽሁፍ ዋናና ቅጂ በማለት ለይተው ማቅረብ አለባቸው።

4.4. በማሸጊያ ፖስታ ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስፈር ያስፈልጋል።

ሀ. የጨረታው ዓይነትና ቁጥር፣

ለ. ጨረታውን ያወጣው መ/ቤት ሥምና አድራሻ፣

ሐ. የተጫራቹ ስም፣ፊርማና ሙሉ አድራሻ፣

መ. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናውን ከዋጋ ማቅረቢያው ጋር አብሮ በማሸግ ወይም በጥሬ ገንዘብ ከሆነ በመ/ቤቱ ህጋዊ ሰነድ ገቢ ተደርጎ መቅረብ ይኖርበታል።

4.5. በፖስታ የሚላክ የመጫረቻ ሰነድ በመዘግየቱና በጥንቃቄ ካለመታሸጉ ጋር በተያያዙ ችግሮች ገዥው መ/ቤት ኃላፊነቱን አይወስድም።

4.6. በማንኛውም ሁኔታ ማንኛውም ተጫራች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ተንተርሶ /ተመስርቶ/ መጫረት አይችልም።

## 5. የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ

5.1. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተገለፀው የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በፊት የመጫረቻ ሰነዱን በተዘጋጀው የጨረታ ቦታ እና የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። ሆኖም የመጫረቻ ሰነዶች ብዛት ያላቸው በመሆናቸው በጨረታ ሳጥኑ ማስገባት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ለ--------------------- ማስረከብ ይችላሉ። ተረካቢውም የተጫራቹን ሥምና አድራሻ እንዲሁም የተረከበበትን ቀንና ሠዓት የሚገልፅ ማስረጃ/ደረሰኝ ይሰጣል፤

5.2. በጨረታ ሰነዱ መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት ደርሶ የጨረታ ሣጥን ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ሳይከፈት ወዲያውኑ ለተጫራቹ (ለአቅራቢው) ተመላሽ ይደረጋል።

## 6. ራስን ከጨረታ ስለማግለል

6.1 ተጫራቾች የጨረታ ሳጥኑ ከመዘጋቱ ------ቀናት በፊት ራሳቸውን ከጨረታው ማግለል ይችላሉ። ስለሆነም ራሳቸውን ከጨረታው ስለማግለላቸው በፖስታ አሽገው በጨረታ ሳጥኑ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

6.2 የጨረታ መዝጊያ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም።

## 7. ጨረታን መክፈት፣ መገምገምና አሸናፊውን መለየት

7.1 ጨረታው በ------------------ክፍል ቢሮ ቁጥር -----------ቀን ------ዓ.ም በ------ሠዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው (የውክልና ማስረጃ በመያዝና ፎቶኮፒውን በማስረከብ) በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል። ሆኖም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ጨረታው በሚከፈትበት ቦታ፣ ቀንና ሠዓት በራሳቸው ምክንያት ባይገኙ የጨረታው ፖስታ እንዲከፈት በማደረግ ውድድሩ ይካሄዳል።

7.2 በጨረታው መክፈቻ ወቅት የተገኙ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በስም መቆጣጠሪያ ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል።

7.3 የተጫራቾች ሥም፣ በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ስለመኖሩ፣ በዘመኑ ግብር የተከፈለ ስለመሆኑ፣ በጨረታው የቀረበው የዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነትና መጠን፣ ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለ መጠኑንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ዓይነትና መጠን እንዲሁም ሌሎች እጩ ተወዳዳሪዎች ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች መሠረታዊ ነጥቦች በንባብ በጨረታው መክፍቻ ወቅት ለተጫራቾች ይገለፃሉ።

7.4 በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የግዥ ኦፊሰሮች የጨረታ መክፈቻ ቃለ-ጉባኤ ይዘጋጃል።

7.5 በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የቀረቡትን የጨረታ ሰነዶች በመገምገም ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከተጫራቾች ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም የሚጠየቀውና የሚሰጠው ማብራሪያ በሁሉም ተጫራቾች እንዲታወቅ በፅሁፍ ሆኖ ተጫራቾች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋውን ወይም የሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለውጡ ማለትም በሌሎች ተፎካካሪ አቅራቢዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ መሆን የለባቸውም።

7.6 በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጁና በግዥ መመሪያው መሰረት ልዩ አስተያዬት እንዲደረግላቸው የተፈቀደላቸው አቅራቢዎች ልዩ አስተያዬቱ ታሳቢ ይደረግላቸዋል።

7.7 በግምገማ ወቅት በነጠላ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋ መካካል የዋጋ ልዩነት ቢኖር በነጠላው ዋጋ መሠረት በማስተካከል ይገመገማል።

7.8 በግምገማ ወቅት ዋጋው በአኃዝና በፊደል በሚገለጽበት ወቅት ልዩነት ቢኖር በፊደል በተገለጸው መሠረት በማስተካከል ይገመገማል።

7.9 በተለየ ሁኔታ የቴክኒክ መገምገሚያ መስፈርት የማያስፈልጋቸው የሆኑ የዕቃ/የአገልግሎት ግዥ ሲገዋም በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ዝርዝር ስፔስፊኬሽን ያሟላ ሆኖ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል።

## 8. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ

8.1 በጨረታ የተወዳደረው አቅራቢ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፈለገውን አነስተኛ የጥራት መመዘኛ መስፈርት ያላሟላ በመሆኑና ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

8.2 ተጫራቹ በአንዱ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋው መካከል የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል ሲሆን፣

8.3 ተጫራቹ ያቀረበው የመጫረቻ ሰነድ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ፣

8.4 ተጫራቹ በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር(TIN) እና የዘመኑን ግብር የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀቶች ያላቀረበና እንደሆነ፣

8.5 ተጫራቾች የግዥ አካሄዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፣

8.6 ጨረታው ተከፍቶ አሸናፊው እስከሚታወቅ ጨረታውን ለማሸነፍ እንዲረዱት ከማንኛውም ኃላፊና ሠራተኛ መደለያ የሰጠ ተጫራች፣

8.7 የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ያላስያዘ እንደሆነ ፣

8.8 ቀደም ሲል በወጡ ጨረታዎች የገባውን የውል ግዴታ ባለማክበሩ በመንግስት ጨረታዎች እንዳይሳተፍ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስታት የታገደ ከሆነ፣

8.9 የመንግስትን የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ፣ የግዥ መመሪያ እና ይህን የጨረታ ሰነድ የሚጥሱ ድርጊቶች መፈፀሙ የተረጋገጠ ከሆነ፣

8.10 እህት ድርጅቶች በጨረታ ውድድር ውስጥ ተሳትፈው ከተገኙ፣

8.11 በጋራ ወይም በሽርክና የሚወዳደሩ ድርጅቶች የተደራጁበት ህጋዊ ሰነድ ማቅረብ ካልቻሉ፣

8.12 ጨረታውን ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታ ውጭ እንዲሆኑ ከመደረጋቸው በተጨማሪ በመንግስት የግዥ ጨረታ ከ2 ዓመት ላላነሰ ጊዜ እንዳይሳተፉ ይደረጋል፣

## 9. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

9.1 የመጫረቻ ሰነድ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ለ---------ቀናት ፀንቶ ይቆያል።

9.2 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲራዘምለት ከፈለገ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በጽሑፍ በመጠየቅ ስምምነት ማግኘት አለበት። ሆኖም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ካልተስማሙ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲሰረዙ ይደረጋል።

9.3 የቀረበላቸውን የመጫረቻ ሰነድ የመቆያ ጊዜ ማሻሻያ ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች መቀበላቸውን እና ጊዜውን በመጥቀስ በጽሁፍ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። በተመሣሣይ ሁኔታ ለዚህ ጨረታ ያስያዙት ዋስትና መቆያ ጊዜ አብሮ እንዲሻሻል ማድረግ ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው። የጨረታ ዋስትናውን ያላሻሻለ ተጫራች የጨረታ ሰነዱን ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውጭ ይደረጋል።

## 10.የጨረታ ውጤትን ስለመግለፅ እና የውል ስምምነት ስለመግባት

10.1 ማንኛውም የጨረታ ግምገማ ውጤት በሚመለከታቸው አካላት በፀደቀ በዕለቱ በጨረታ አሸናፊ ለሆነው ተጫራች እና በጨረታው ተሣታፊ ለሆኑ ሌሎች ተጫራቾች የተሸነፉበትን ምክንያት በማካተት በእኩል ጊዜ ለሁሉም በጽሁፍ ይገለፃል፣

10.2 አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ እንደተገለጸለት የውል ማስከበሪያ ዋስትና እና የመሳሰሉትን በማመቻቸት የአቅርቦት ውል ስምምነት ለመፈፀም መዘጋጀት አለበት።

10.3 አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ እና የግዥ ውል እንዲፈጽም ከመ/ቤቱ ደብዳቤ በደረሰው ከ5 የሥራ ቀናት ቀናት በኋላ ባሉት በ5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የአቅርቦት ውል ከግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ጋር መፈራረም አለበት።

10.4 በጨረታ ማስታወቂያ የተጠየቀውን የዕቃ ወይም አገልግሎት መጠን 20% በመጨመር ወይም በመቀነስ በግዥ ፈጻሚ መ/ቤትና በአቅራቢው መካከል የውል ስምምነት በሚፈፀምበት ወቅት ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የማስተካከል መብት አለው። ሆኖም በአቅርቦት ወቅት የአቅርቦት መጠን ለውጥ ማድረግ ከፈለገ ለአቅራቢው ድርጅት ከ-----ቀናት በፊት በጽሁፍ በመግለጽ አቅራቢው ሲስማማ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

10.5 አሸናፊው የዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት እንደታወቀና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የውል ስምምነት እንደተፈፀመ የተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ይመለሳል።

10.6 አሸናፊው ተጫራች በጨረታው ወቅት ቅድሚያ ክፍያ እንደሚፈልግ ነጥብ አስይዞ ከሆነ ለሚያቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት እስከ ብር ----- ወይም የዕቃውን ወይም አገልግሎት ዋጋ -----% የሚደርስ ቅድሚያ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል። ሆኖም ቅድሚያ ክፍያው የሚሰጠው ከጠየቀው

የቅድሚያ ክፍያ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ ባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ /ሲ.ፒ.ኦ/ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና /Unconditional Bank Guarantee/ ማቅረብ ሲችል ብቻ ነው።

10.7 በ10 .6 የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የግንባታ ኩባንያዎች እና የመድሐኒት አምራች ኢንዱስትሪዎች በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ:: በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ዋስትና የሚጠቀሙ ከሆነ ውል ሰጪው ግዥ ፈጻሚ አካል እና ውል ተቀባይ የሆነው አቅራቢ የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለባቸው።

## 11.የግዥ ውል ማስከበሪያ /ፐርፎርማንስ ቦንድ/

11.1 አሸናፊው ተጫራች የውል ስምምነት እንዲፈፅም በተገለፀበት ጊዜ ውስጥ ከአሸነፈበት የዕቃ/የአገልግሎት ጠቅላላ ዋጋ 10% / የተሽከርካሪ ኮንትራት ጥገና ከሆነ 3%/ የግዥ ውል ማስከበሪያ (ፐርፎርማንስ ቦንድ) በታወቀ ባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ /ሲ.ፒ.ኦ/ ወይም በጥሬ ገንዘብ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና /Unconditional Bank Guarantee/ ማስያዝ ይኖርበታል። ከአሸናፊው የሚቀርበው የዉል ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ ውሉ ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 30 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል::

11.2 በ11.1 የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የግንባታ ኩባንያዎች እና የመድሐኒት አምራች ኢንዱስትሪዎች በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ::

11.3 በጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች የአቅርቦት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ገዥው የጨረታ ማስከበሪያውን በመውረስ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ገምግም ካመነበት በውድድር ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ይችላል። በጨረታ ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ መ/ቤቱ የመውረስ መብት አለው።

11.4 አቅራቢው በገባው የውል ስምምነት መሠረት የዕቃውን ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ጠብቆ በውሉ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካላቀረበ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በካሳ መልክ የውል ማስከበሪያውን ያስቀራል ወይም ይወርሳል።

11.5 በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት እና አቅራቢው መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ ዋስትና አቅራቢው የውል ግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ ይመለሳል።

## 12.የርክክብ ጊዜና ቦታ

አሸናፊው አቅራቢ አሸናፊነቱ በደብዳቤ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ----------ቀናት ውስጥ --------- ----------------------------------ድረስ አጠቃሎ የማቅርብ ግዴታ አለበት።

## 13. አቤቱታ ስለማቅረብ

13.1 በጨረታ ሂደቱ ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል የሚል ወይም በጨረታው ግምገማ ውጤት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት በ5 የሥራ ቀናት ውሰጥ ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በጽሑፍ ቢሮ ቁጥር -------ድረስ ማቅረብ ይችላል፣

13.2 አቤቱታው የቀረበበት መ/ቤትም ምላሹን በቀረበለት በ4 የሥራ ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው መልስ ይሰጣል።

13.3 ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ አቅራቢ አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አካላት ማቅረብ ይችላል፣

13.4 በየደረጃው በሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አካላቱ ውሳኔ ላይ ያልረካ አቅራቢ በፍርድ ቤት ክስ ሊመሰርት ይችላል፣

13.5 በዚህ አንቀፅ ተ.ቁ 13.1. ከተሰጠው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፣

# ክፍል 2. አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች

## 1. ትርጓሜ

በዚህ ውልየሚከተሉት ቃላቶች የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል።

1.1 “ውል” ማለት በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት (ውል ሰጭ) እና አቅራቢ (ውል ተቀባይ) መካከል የተገባውን እና ተዋዋዮች የፈረሙበት ሰነድ ሲሆን ከውሉ ጋር የተያያዙትን እንዲሁም በውሉ የተጠቀሱትን ሰነዶች ሁሉ ይጨምራል።፡

1.2. “የውል ዋጋ” ማለት አቅራቢው እንደ ውሉ ግዴታውን አሟልቶ እና በአግባቡ ሲፈጽም በውሉ መሠረት የሚፈጸምለት ክፍያ ነው።

1.3. “አቅርቦት” ማለት በዚህ ውል መሰረት ዕቃ አቅራቢው ለገዥው መ/ቤት የሚያቀርበው ዕቃ ነው።

1.4. “የግዥ ፈጻሚ መ/ቤት” ማለት ዕቃን ለመግዛት ጨረታውን የሚያወጣው፣ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የግዥ ውል ስምምነት የሚፈፅም እና ለዕቃ አቅራቢው ክፍያ የሚፈጽም የመንግስት መ/ቤት ነው።

1.5. “አቅራቢ”ማለት ዕቃን ለግዥ ፋጻሚ መ/ቤት ለማቅረብ የውል ስምምነት የሚፈጽምና በውሉ መሰረትም ዕቃውን በውሉ ውስጥ በተጠቀሰው ቦታና ሰዓት የሚያቀርብ ድርጅት ወይም ግለሰብ ነው።

1.6. “ዕቃዎች” ማለት በዚህ ውል መሰረት አቅራቢው ለገዥው የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና መለዋወጫዎቸ እነዲሁም አገልግሎቶች ናቸው።

## 2. ምርመራና ሙከራ

2.1 አቅራቢው ዕቃዎችን ከማጓጓዙ ወይም ከማስረከቡ በፊት በራሱ ወጭ ምርመራ የማካሄድና ለእያንዳንዱ አቅርቦት ከሚመለከተው አካል የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት።

2.2 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ወይም ወኪሉ ዕቃዎቹ እንደ ውሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ምርመራ ወይም ሙከራ የማድረግ መብት አለው።የቴክኒካል መግለጫው /ስፔስፊኬሽን/ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ምን ዓይነት ምርመራና ሙከራ እንደሚፈልግ እና የሚደረግበትንም ቦታ በግልፅ ያስቀምጣል። ለምርመራውና ለሙከራው ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የሚወክለውን ለአቅራቢው በጽሁፍ ያስታውቃል።

2.3 ምርመራና ሙከራ በሚደረግበት ጊዜ አቅራቢው ያለ ምንም ክፍያ ተገቢ የሚባሉ ዕገዛዎችን፣ ምቹ ሁኔታዎችን እንዲሁም ስዕሎችንና የምርት መረጃዎችን ለመርማሪዎች ያቀርባል።

2.4 በምርመራ ወይም በሙከራ መሰፈርቱን የማያሟሉ ሆነው የሚገኙ ዕቃዎችን ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርግ የሚችል ሲሆን አቅራቢው በራሱ ወጭ የመተካት ወይም የመለወጥ ኃላፊነት ይኖርበታል።

2.5 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ወይም ወኪሉ አስቀድሞ መመርመሩ፣ መሞከሩና ማሳለፉ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ዕቃዎችን ከተረከበ በኋላ ያለውን የመመርመር፣ የመሞከርና መስፈርቱን የማያሟሉትን ውድቅ የማድረግ መብቱን ሊገድብ ወይም ቀሪ ሊያደርግ አይችልም።

## 3. አገልግሎቶች

3.1 አቅራቢው በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ፍላጎት የሚከተሉትን አገልግሎቶች እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል።

ሀ. የቀረቡትን ዕቃዎች የመገጣጠም ወይም ሥራ የማስጀመር አገልግሎት ወይም ቦታውን የመጎብኘት፣

ለ. የቀረቡትን ዕቃዎች ለመገጣጠም ወይም ለመጠገን የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን እንዲያቀርብ

ሐ. ለቀረቡ እያንዳንዱ ዕቃዎች ሥራ ለማስጀመርም ሆነ ለማስጠገን የሚውለውን ማንዋል እንዲቀርብ፣

መ. በውሉ ለተጠቀሰው ጊዜ ያህል ዕቃዎችን የመጠገን ወይም ቦታውን የመቆጣጠር /የመመልከት/ ተግባራትን መፈፀሙ አቅራቢው በውሉ ከተጣሉት ግዴታዎች ውጭ ሊያደርገው አይችልም፣

ሠ. የቀረቡትን ዕቃዎች የመገጣጠም፣ ሥራ የማስጀመር፣ የአጠቃቀም ሁኔታውን የማሳዬት፣ ጥገናን አስመልክቶ የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱን  የሰው ኃይል የማሰልጠን፣

ከዚህ በላይ ለተመለከቱት አገልግሎቶች ክፍያ በውሉ ባልተመለከተ ጊዜ አቅራቢውና ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ስለ ክፍያው አስቀድመው የሚስማሙ ሲሆን ክፍያውም አቅራቢው ለአገልግሎቱ ለሌሎች ወገኖች ከሚያስከፍለው ሊበልጥ አይችልም።

## 4. የዋስትና ኃላፊነት

4.1 እንደአስፈላጊነቱና እንደ ዕቃው ባህሪ አቅራቢው የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ያላገለገሉ፣ አዲስ፣ ንድፍ፣ በቁሳቁስ በጣም የቅርብ ጊዜ መሻሻሎች ስለመሆናቸው ዋስትና ይወስዳል። ከዚህም በተጨማሪ አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ከንድፍ፣ ከተሰሩበት ቁስ ወይንም ከአምራቹ የሚመነጭ ጉድለት እንዳይኖርባቸው ኃላፊ ነው።

4.2 አቅራቢው የወሰደው የዋስትና ኃላፊነት ማናቸውም የዕቃ ክፍል ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለዚሁ የቀረበ ዕቃ ለ------- ወራት የፀና ይሆናል።

4.3 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ከዋስትና ኃላፊነት ጋር በተያያዘ የሚያነሳው የመብት ጥያቄ ካለ ለአቅራቢው ሳይዘገይ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4.4 የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የመብት ጥያቄ እንደደረሰው አቅራቢው ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በሚወስነው ጊዜ ውስጥ በራሱ ወጭ ጉድለት ያለበትን ዕቃ መጠገን ወይም በሌላ የመተካት ኃላፊነት አለበት።

4.5 አቅራቢው ጉድለት ያለበትን ዕቃ እንዲስተካከል ተነግሮት በተገለፀለት ውስጥ መፈጸም ካልቻለ፣ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ያሉት ሌሎች መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በአቅራቢው ኃላፊነትና ወጭ ተገቢ የሆነውን የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

## 5. ክፍያ

5.1 በውሉ መሰረት ለአቅራቢው የሚፈፅመው ክፍያ ዕቃዎችን አሟልቶ እንደቀረበ የሚቀነስበት ቅድመ ክፍያ ካልኖረ በቀር 100% ይፈፀምለታል።

5.2 ክፍያው በባንክ አማካኝነት እንዲፈፀምለት አቅራቢው የሚፈልግ ከሆነ ለባንክ አገልግሎት የሚወጣውን ወጭ አቅራቢው ይሸፍናል።

5.3 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ከሚፈፅመው ክፍያ ላይ ደረሰኝ በመስጠቱ የቅድመ ክፍያ ታክስ /WITH HOLDING TAX/ ታክስን ይዞ የማቆዬት መብት አለው።

## 6. ዋጋ

6.1 አቅራቢው ለሚያቀርበው ዕቃ እና ለሚፈጽመው አገልግሎት የሚጠይቀው ዋጋ አቅራቢው በጨረታው ከገለጸውና አሸናፊ ከሆነበት ሊለይ አይችልም።

## 7. የውል ማሻሻል

7.1 በተዋዋይ ወገኖች በተፈረመ የጽሁፍ ማሻሻያ ካልሆነ በቀር በውሉ ላይ አንዳችም ለውጥ ወይም መሻሻያ አይደረግም።

## 8. ግዴታን ስለማስተላለፍ

8.1 የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የጽሁፍ ስምምነት አስቀድሞ ካላገኘ በቀር፣ አቅራቢው በውሉ መሰረት ሊፈፅማቸው የሚገቡ ግዴታዎችን በሙሉም ሆነ በከፊል ለሌላ አካል ለማስተላለፍ አይችልም።

## 9. የአቅራቢው አፈፃፀም መዘግዬት

9.1 አቅራቢው ዕቃዎችን የሚያቀርበውና አገልግሎቶችን የሚሰጠው በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይሆናል።

9.2 ይቅርታ የማያሰጡ በአቅርቦት ሂደት የሚገጥም መዘግዬት አቅራቢውን ለሚከተሉት ቅጣቶች ሊዳርጉት ይችላሉ።

ሀ. ለውል ማስከበሪያ ያስያዘውን የዋስትና ገንዘብ ወይም መያዣ መውረስ፣

ለ. የጉዳት ካሳ መቀጮ እና ወይም

ሐ. እንደዉሉ ባለመፈጸም የውሉ መቋረጥ

9.3 በውሉ አፈፃፀም ሂደት በማናቸውም ጊዜ አቅራቢው ወይም የእሱ ንዑስ ተዋዋይ የዕቃ አቅርቦትን ወይም የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያስተጓጉል ሁኔታ የገጠማቸው እንደሆነ አቅራቢው ወዲያውኑ በጽሁፍ የመዘግየቱን፣የሚቆይበትን ጊዜና ምክንያቶቹን ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት። የአቅራቢውን ማስጠንቀቂያ የተቀበለ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ሁኔታውን ወዲያውኑ በመገምገም የአቅራቢውን የማቅረቢያ ወይም የመፈፀሚያ ጊዜ ሊያራዝምለት የሚችል ሲሆን ማራዘሚያውን ውሉን በማሻሻል ዓይነት በተዋዋዮቹ ሊፀድቅ ይገባል።

## 10. የጉዳት ካሳ

10.1. አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃዎችን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሁም የሚፈለግበትን አገልግሎት ለማቅረብ ወይም ለመፈጸም ያልቻለ እንደሆነ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ያሉት ሌሎች መፍትሂዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ለአቀረበው ዕቃ ወይም ላልተፈፀመው አገልግሎት ከሚከፍለው ዋጋ ላይ 10% እስከሚደርስ ድረስ ለእያንዳንዱ ቀን 0.1% (1/1000)ተቀናሽ ማድረግ ይችላል።

10.2. የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል የመቀጫው መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ መጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ ይችላል፣

## 11. ውልን ስለማቋረጥ

11.1 በውሉ መጣስ የሚኖሩት ሌሎች መፍትሂዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለአቅራቢው በመስጠት በሚከተሉት ምክንያቶች ውሉን በሙሉ ወይም በከፊል ማቋረጥ ይችላል።

ሀ. በውሉ በተመለከው መሰራት በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በተሰጠው የማቅረቢያ ወይም ተጨማሪ ጊዜ ከተሰጠ የማራዘሚያ ጊዜ ውስጥ አቅራቢው ዕቃዎችን በሙሉ ወይም ከፊሉን ማቅረብ ባልቻለ ጊዜ ወይም፣

ለ. አቅራቢው በውሉ የተመለከቱትን ሌሎች ግዴታዎች መፈጸም ባልቻለ ጊዜ ነው፣

11.2 በአቅራቢው ችግር አማካኝነት ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ውሉን በሙሉ ወይም በከፊል ባቋረጠ ጊዜ፣ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ እንደአግባቡ ያልቀረቡትን ዕቃዎች ተመሳሳይ መግዛት የሚችል ሲሆን ተጨማሪ ወጭ ቢኖር አቅራቢው ኃላፊ ይሆናል። ይህ ሲሆን ባልተቋረጠው የውል አካል መሠረት አቅራቢው መፈፀሙን ይቀጥላል።

## 12. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት

12.1 አቅራቢው ዕቃዎችን ያላቀረበው ወይም ግዴታዎችን ያልፈጸመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሲሆን በዚሁ ልክ ሌላ ለአፈፃፀም ያስያዘው የዋስትና ገንዘብ አይወረስበትም፣ የጉዳት ካሳም አይከፈልም፣በእርሱ ምክንያት ውሉ አይፈርስም።

12.2 ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ እንደገለጸው ዓይነት ይሆናል።

12.3 ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ስለ ሁኔታውና ስለ ምክንያቱ አቅራቢው ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ወዲያውኑ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል። ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ በጽሁፍ ካልታዘዘ በቀር አቅራቢው የሚቻለውን ያህል የውሉን አፈጻጸም መቀጠል የሚኖርበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ያልተስተጓጎሉ አማራጭ የአፈፃፀም ዘዴዎችንም መፈለግ ይኖርበታል።

## 13. አለማግባባትን ስለመፍታት

13.1 በዚህ ውል ወይም ከውሉ ጋር በተያያዘ የሚነሳ አለመግባባት ቢኖር ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ አቅራቢው በቀጥታ ወይም 3ኛ ወገን ባለበት ውይይት በስምምነት ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለባቸው፣

13.2 በቀጥታ ወይም 3ኛ ወገን ባለበት የሚደረገው ውይይት በተጀመረ በ----- ቀናት ለአለመግባባቱ ሰላማዊ መፍትሄ ማስገኘት ያልቻለ እንደሆነ ከተዋዋዮቹ አንዱ አለመግባባትን ውሉ በተፈረመበት ቦታ ወደ ሚገኘው መደበኛ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ይችላል።

## 14. ስለ ቋንቋ

14.1 ውሉ፣ በተዋዋዮች መካከል የሚደረጉ መፃፃፎች ሁሉ እንዲሁም የውሉ አካል የሆኑ ሰነዶች በአማርኛ ይሆናሉ። ሆኖም በእንግሊዝኛ የሚጻፍ ከሆነ ወደ አማርኛ የሚተረጎም ይሆናል።

14.2 በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል አለመጣጣም ሲያጋጥም የአማርኛው ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 15. ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎች

ውሉ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰረባቸው ሕጎች አግባብ የሚተረጎም ይሆናል፡፡

# ክፍል 3

# የዕቃና አገልግሎት አቅርቦት ውል

## 1. ጠቅላላ

ይህ ውል በአንድ በኩል የ-------------------------------- መ/ቤት ስልክ---------------ፋክስ--------ከዚህ ቀጥሎ "ገዥ" /ውል ሰጭ/ እየተበለ በሚጠራው

**እና**

በሌላ በኩል --------------------------------------------------የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ------------ስልክ --------------------ፋክስ ---------------አድራሻ ክልል-----------ዞን-----------ወረዳ-------ቀበሌ-------------የቤት ቁጥር---------------ከዚህ ቀጥሎ "አቅራቢ" /ውል ተቀባይ / እየተበለ በሚጠራው

መካከል ዛሬ -----------------ቀን-------ዓ.ም ---------------------ከተማ ስምምነት የተደረገበት ----------------------------የዕቃና አገልግሎት አቅርቦት ውል ነው፡፡

## 2. የውሉ ዓይነት

2.1 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት -------------------ቀን----------ዓ.ም በ----------------------------ጋዜጣ ባወጣው የጨረታ ቁጥር-----------መሠረት አቅራቢ አሸናፊ የሆነባቸውን የሚከተሉት ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለማቅረብ ተስማምቷል፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫትን/VAT/ ጨምሮ | | ጠቅላላ ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| የግዥ ውል የተያዘበት ጠቅላላ ዋጋ | | | | | | | |

ከላይ በሰንጠረዥ የተጠቀሰው የዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶች ዋጋ የጉምሩክም ሆነ ማንኛውምና የታክስና የትራንስፖርት ክፍያዎችን ወይም ወጭዎችን ያካትታል፡፡

## 3. የክፍያ አፈፃፀም

3.1 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት------------% ለአቅራቢ ቅድሚያ ክፍያ ይከፍላል። ሆኖም ከሚከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ጋር እኩል ዋጋ ያለው በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ስም የተዘጋጀ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ ቼክ /ሲ.ፒ.ኦ/ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማስያዝ ያለበት ሲሆን ይኸውም የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና የቆይታ ጊዜ ከውል ዕድሜው እኩል ሊሆን ይገባዋል።

3.2 ቀሪውን -------------% ክፍያ የዕቃው ርክክብ ተጠናቆ ማስረጃ ሲቀርብ ይፈፀማል።

3.3 ክፍያው እንደ አቅራቢው ምርጫ በቼክ ይከፈላል ወይም በ------------------ንግድ ባንክ በ-------------ቅርንጫፍ በ------------------ሂሳብ ቁጥር ገቢ ይደረጋል። ክፍያው በባንክ የሚተላለፍ ከሆነ የባንክ አገልግሎት ክፍያ በአቅራቢ ይሸፈናል።

## 4. ርክክብ

4.1 አቅራቢ በውሉ ላይ የተጠቀሱትን ዕቃዎች በሙሉ እስከ-----------ቀን------ዓ.ም ድረስ ለማሰረከብ ተስማምቷል።

4.2 የርክክብ ቦታው በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ዋናው መጋዘን ባለበት-----------------ቦታ--------- ይሆናል።

4.3 በርክክብ ወቅት ዕቃዎችን ለማራገፍ /ለማውረድ/ የሚጠየቀው ወጭ አቅራቢ ይሸፍናል።

## 5. ጥራትና ዋስትና

5.1 አቅራቢ በውል በተጠቀሰው ዝርዝር መግለጫና ባቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ መሠረት የተመለከቱትን አዲስ ዕቃዎች ማስረከብ አለበት። ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶች በውሉና አቅራቢ ባቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ላይ የተጠቀሰውን ዝርዝር መግለጫ /Specification/ የማያሟሉ እንዲሁም አዲስና ትክክለኛ አለመሆናቸውን ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በሚመርጠው ወይም በሚመለከተው ባለሙያ ቢረጋገጥ ተቀባይነት አይኖራቸውም።

5.2 አቅራቢ ለሚያስረክባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች የሰጠው የዋስትና ጊዜ፣ ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶች ርክክብ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ለ----- ወራት ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ዕቃዎቹ በአመራረት ችግር ምክንያት በፍተሻ ወቅት ቢበላሹ ወይም ከጥቅም ውጭ ቢሆኑ ወይም የአመራረትና የጥራት ጉድለት ወይም ችግር ያለባቸው መሆኑ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በሚመርጠው ወይም በሚመለከተው ባለሙያ ሲረጋገጥ አቅራቢው በተገለፀበት --------ቀናት ውስጥ ለመተካት ተስማምቷል።

5.3 አቅራቢ የሚያቀርባቸው ዕቃዎች በስፔስፊኬሽኑ መሠረት አለመሆናቸው በፍተሻ /በኢንስፔክሽን/ ቢረጋገጥ ለፍተሻው የሚከፈል ወጭ በአቅራቢ ይሸፈናል።

## 6. የተዋዋዮች መብትና ግዴታዎች

### 6.1 የግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ውል ሰጭ/ ግዴታዎች

6.1.1 አቅራቢ/ውል ተቀባይ/ ሊያቀርብ ውል የገባበትን ዕቃ አስቀድሞ በተቀመጠለት ዝርዝር ዓይነትና ጥራት አሟልቶ ማቅረቡን በባለሙያ በማረጋገጥ ዕቃው ውል ተቀባይ/አቅራቢ/ በተገኘበት ተመርምሮ ይረከባል።

6.1.2 በቁጥር 6.1.1 የተመለከተው እንደተፈጸመ ወድያውኑ የዕቃውን ዋጋ ---------------እና የውል ማስከበሪያ ዋስትናውን ለውል ተቀባይ ያስረክባል።

### 6.2 የግዥ ፈጻሚ መ/ቤት /የውል ሰጭ/ መብቶች

6.2.1 ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በጨረታው ዝርዝር መሠረት ከውል ተቀባይ ዕቃውን በተወሰነው የጊዜ ገደብ የመረከብ መብት አለው።

6.2.2 አቅራቢ/ውል ተቀባይ/ ዕቃውን አሟልቶ ሲያቀርብለት እንዲመረመር በሚመደበው ባለሙያ አማካኝነት ምርመራው እየተረጋገጠ ርክክብ እንዲፈፀም የመጠየቅ መብት አለው። የምርመራ ወጭውም በውል ተቀባይ የሚሸፈን ይሆናል።

6.2.3 በርክክብ ወቅትና ከርክክብ በኋላ የሚታይ የዕቃ ጥራት መጓደል ወይም ለተገቢው ሥራ ላይ የመዋል ችግር ካጋጠመው በውል ተቀባይ ወጭ ጉድለት ያለበት ዕቃ እንዲተካ እና የመስራት ችግር ያለበት ዕቃ እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት አለው።

6.2.4 የተከሰተው የጥራት መጓደል ወይም ችግር እንዲታረም በጽሁፍ ለውል ተቀባይ ተገልጾለት ጉድለቱ ሳይተካ ወይም ችግሩ ሳይስተካከል 15 ቀናት ካለፈ ጉድለት ወይም ችግር የታዬበትን ዕቃ ለውል ተቀባይ ተመላሽ የማድረግ ወይም ጉድለቱ እንዲተካ እና ችግሩ እንዲስተካከል ለማድረግ ይችላል።

6.2.5 ከላይ በንዑስ ቁጥር 6.2.4 እንደተመለከተው ጉድለት ያለበትን ወይም ችግር የታየበትን ዕቃ ተመላሽ ካደረጉ እና ውል ሰጭው የዕቃውን ጠቅላላ ዋጋ ክፍያ ያልፈፀመ እንደሆነ ተመላሽ የተደረገው ዕቃ ዋጋ ቀንሶ ያስቀራል። ነገር ግን ክፍያ ፈጽሞ ከሆነ ተመላሽ የሚደረጉት ዕቃዎች ዋጋ ተመላሽ እንዲደረግለት ውል ሰጭው የመጠየቅ መብት አለው።

6.2.6 ከላይ በንዑስ ቁጥር 6.2.4 እንደተመለከተው ጉድለት ያለበትን ወይም ችግር የታየበትን ዕቃ ውል ሰጭው እንዲተካ ወይም እንዲስተካከል ያደረገ እንደሆነ ለማስተካት ወይም ለማስተካከል የወጣ ተጨማሪ ወጭ ሁሉ ከውል ተቀባዩ ላይ የሚጠየቅ ይሆናል።

### 6.3 የአቅራቢ/ ውል ተቀባይ/ ግዴታዎች

6.3.1 ውል ተቀባይ በጨረታ አሸንፎ ውል የፈረመበትን አዲስ ዕቃ በጨረታ ሰነዱ በተመለከተው ዝርዝር ሁኔታ /Specification/ ከነአስፈላጊ ቁሳቁሶች /Accessories/ በ----------ቀናት ውስጥ እስከ----------ቀን------ዓ.ም ድረስ በማቅረብ ለውል ሰጭ ያስረክባል።

6.3.2 ውል ተቀባይ ለውል ሰጭ ከዕቃዎች ጋር ሊተላለፍ የሚገባውን የባለቤትነት ወይም የባለይዞታነት ማስረጃ ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን ለውል ሰጭ ወዲያውኑ ያስተላልፋል።

6.3.3 ውል ተቀባይ ለውል ሰጭ በሚያቀርባቸው ዕቃዎች ላይ ለሚፈለገው አገልግሎት የማያበቃ የጥራት መጓደል ወይም የመስራት ችግር ቢስተዋልባቸው ውል ተቀባይ ኃላፊ ሆኖ ይቆያል።

6.3.4 የጥራት ጉድለት ወይም የመስራት ችግር የታየባቸው ዕቃዎች ለውል ተቀባይ እንደተገለፁለት በአፋጣኝ ይተካል።

6.3.5 ውል ተቀባይ ዕቃውን የሚያቀርበው ምርመራ በማከናወን ሲሆን የሚያስረክበውም በውል ሰጭ አድራሻ ነው።

6.3.6 ውል ተቀባይ በጨረታው በተመለከተው ጊዜ ዕቃውን ለውል ሰጭ ለማስረከብ የሚያስችል በፍታብሔር ህጉ የተመለከተው ዓይነት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥመው ወዲያውኑ ለውል ሰጭ ያስታውቃል።

6.3.7 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 6.3.6 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ወይም በሀገሪቱ በሚፈጠር የዋጋ ንረት ምክንያት በጨረታ ሰነዱ ከተመለከተው ውጭ ውል ሰጭውን ሊጠይቅ አይችልም።

### 6.4 የአቅራቢ/ የውል ተቀባይ/ መብቶች

6.4.1 ውል ተቀባይ ዕቃውን አጠናቆ እንዳስረከበ የዕቃው ጠቅላላ ዋጋ ክፍያ ይፈፀምለታል።

6.4.2 ከላይ በንዑስ ቁጥር 6.4.1 የተመለከተው እንደጠበቀ ሆኖ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበው ማስያዣ ይለቀቅለታል።

## 7 የውል ማስከበሪያ ዋስትና

7.1 አቅራቢ ውል የገባባቸውን ዕቃዎች አጠቃላይ ዋጋ 10% በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት /ውል ሰጭ/ ስም ተዘጋጅቶ የውል ማስከበሪያ ዋስትና **በባንክ በተረጋገጠ ቼክ/ ሲ.ፒ.ኦ/** ወይም **በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና** ወይም **ጥሬ ገንዘብ** አስይዟል።

7.2 አቅራቢው ዕቃዎቹን በጊዜ ገደቡ መሰረት አሟልቶ ካላቀረበ እንዲሁም በውሉ ላይ የተጠቀሱ ሌሎች ግዴታዎችን ካልተወጣ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት የውል ማስከበሪያውን በሙሉ የመውረስ መብት አለው።

## 8 የአቅርቦት ማዘግዬት ቅጣት

አቅራቢ በውሉ ላይ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን አጠቃሎ ባያስረክብ ከማስረከቢያው የመጨረሻ ቀን ማግስት ጀምሮ ለእያንዳንዱ ላዘገየበት ቀን ዘግይተው የቀረቡ ዕቃዎችን ጠቅላላ ሽያጭ ዋጋ 0.1% ወይም 1/1000 በየቀኑ እየተቀጣ ለ------------ ቀናት ጊዜ ቅጣት ለመክፈል የተስማማ ሲሆን ከ---------------ቀናት በኋላ ውሉ እንደተሰረዘ ይቆጠራል። ቅጣት ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ይከፈላል። ሆኖም በውሉ ላይ በተገለፀው ጊዜ ገደብ አቅራቢ ካላቀረበ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ውሉን የማፍረስና የውል ማስከበሪያውን የመውረስ መብት አለው።

## 9 የጉዳት ካሳ

አቅራቢ ውል የገባበትን ዕቃ በከፊልም ሆነ በሙሉ በማቅረቢያ ጊዜው ማቅረብ ካልተቻለ በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ለዋስትና ያስያዘው 10% እስኪ ደርስ ድረስ ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ይከፈላል።

## 10 ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ስለማሳወቅ

አቅራቢ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ውሉን ተግባራዊ ለማድረግ ካልተቻለ ይኸው ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በተከሰተ በ--------ቀናት ውስጥ ለግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በጽሁፍ በማሳወቅ ሁኔታው በአግባቡ እልባት እንዲያገኝ ያመቻቻል። አቅራቢው ይህንን ባለማድረጉ ምክንያት ለሚደርሰው ኪሳራ ኃላፊ ይሆናል።

## 11 ስለ ድርድር ዳኝነት

በዚህ ውል አፈፃፀም ሂደት በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት እና በአቅራቢ መካከል አለመግባባት ከተፈጠረ ተዋዋይ ወገኖች የተፈጠረውን ችግር በድርድርና በመግባባት ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ።

በግዥ ፈጻሚ መ/ቤት በአቅራቢ መካከል የተፈጠረውን ችግር በዚሁ ውል መሰረት በድርድር መፍታት ካልተቻለ ጉዳዩ የሚታየው የግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ባለበት በአማራ ክልል በ------------------- ከተማ በሚገኙ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች ይሆናል'።

## 12 ስለ መለኪያ፣ የጊዜ አቆጣጠርና የገንዘብ ምንዛሬ

በውሉ ውስጥ የተመለከቱ መለኪያዎች፣ የጊዜ አቆጣጠር እና የገንዘብ ምንዛሬ በኢትዮጵያ የመለኪያ፣ የጊዜ አቆጣጠር እና የገንዘብ ምንዛሬ መሰረት ይሆናል።

## 13 የውሉ አካል ስለሚሆኑ ሰነዶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ሰነዶች የዚህ ውል አካል ናቸው።

ሀ. የጨረታ ማስታወቂያ፣

ለ. ተጫራቾች የተወዳደሩበትና የተመረጡበት ቃለ ጉባኤ፣

ሐ. የውል ተቀባይ አሸናፊነት የተገለፀበት ደብዳቤ፣

መ. የጨረታ አሸናፊው ያቀረበው የውል ዋስትና ገንዘብ፣

ሠ. በውል ሰጭና ተቀባይ መካከል የተፈረመው ይህ የግዥና ሽያጭ ውል፣

ረ. ግዥ ፈፃሚው አካል የሸጠው የጨረታ ሰነድ፣

ሰ. አቅራቢው በጨረታ ወቅት ያቀረበው የመጫረቻ ሰነድ፣

### 14 ተፈፃሚነት ስላላቸው ሕጎች

ውሉን በተመለከተ የሚነሱ ውዝግቦችን ለመፍታት የአማራ ክልል ወይም የፌዴራሉ መንግስት አግባብነት ያላቸው ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ። ሆኖም የክልሉ ሕጎች የተፈፃሚነት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

### 15 የውል ረቂቅን ስለማስመርመር

የሚፈፀመው ውልም ከዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) በስተቀር በየደረጃው ባለ የፍትህ ቢሮ አካል ተመርምሮና ታይቶ ውል እንዲወሰድ መደረግ አለበት።

### 16 ስለእማኞች

በሁሉም ውሎች ውስጥ 2 እና ከዚያ በላይ የሆኑ እማኞች በውል ሰነዱ ላይ ሊፈርሙበት ይገባል።

### 17 የውሉ መጽናት

ይህ ውል ሁለቱ ወገኖች ከተፈራረሙበት ከ-----------------ቀን-----------ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

| <u>ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት (ውል ሰጭ)</u> | <u>አቅራቢ (ውል ተቀባይ)</u> |
|---|---|
| ሥም ---------------------------- | ሥም------------------------ |
| ኃላፊነት ------------------------ | ኃላፊነት -------------------- |
| ፊርማ ------------------------- | ፊርማ ---------------------- |
| ቀን---------------------------- | ቀን------------------------ |

**<u>እማኞች</u>**

| | <u>ሥም</u> | <u>ኃላፊነት</u> | <u>ፊርማ</u> | <u>ቀን</u> |
|---|---|---|---|---|
| 1. | --------------------- | ----------------- | --------------- | ------------------- |
| 2. | --------------------- | ----------------- | --------------- | ------------------- |
| 3. | --------------------- | ----------------- | --------------- | ------------------ |

የሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ክብ ማህተም በእያንዳንዱ ገጽ መስፈር ይኖርበታል።

# ክፍል 4. የጨረታ ቅጾች

ቅጽ -01

## 1. የግዥ ፍላጎት ማቅረቢያ ቅጽ

*የመ/ቤቱ ስም---------------------------------------አድራሻ--------------*

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ዝርዝር መግለጫ /ስፔሰፊኬሽን/ | መለኪያ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሎት-1 | | | | |
| 1.1 | | | | | |
| 1.2 | | | | | |
| 1.3 | | | | | |
| 1.5 | | | | | |
| 2 | ሎት -2 | | | | |
| 2.1 | | | | | |
| 2.2 | | | | | |
| 2.3 | | | | | |
